ቁጥር:- ጎፓ/043/2015
ቀን:- 03/12/2015 ዓ.ም

ለኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት - ቃሊቲ ኦሊሞነሽ 3/12/15
እዲስ አበባ
011 12423 01/03
ጎሬ-ጉጎ

ጉዳዩ:- በጉራጌ የክልል እደረጃጀት ጥያቄ ዙሪያ አሰቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥ የቀረበ አቤቱታ

የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት በህገ መንግስቱ እና በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት መሰረት ከጉራጌ ዞን ምክር ቤት በቀን 04/05/2012 ዓ.ም የቀረበለትን አቤቱታ ወደ ጎን በማድረግ በህዝባችን ላይ እየፈፀመ ያለው በደል እና ህገ መንግስታዊ ጥሰት በማለመልከት 4 ገፅ አቤቱታ ከዚህ ደብዳቤ ጋር እባሪ አድርገን የላከን መሆኑ እየገለፅን አሰቸኳይ ውሳኔ እንዲሰጥ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከሰላምታ ጋር!

መሐመድ አብራር መሐመድ
የጎጎት ፓርቲ ለ[illegible]
Mohammed Ab[illegible]ned
Chairma[illegible]

ጎጎት ለጉራጌ አንድነትና ፍትህ ፓርቲ
Gogot Unity [illegible]

ቁጥር:- ጎፓ/042/2015
ቀን:- 03/12/2015 ዓ. ም

ለኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት
አዲስ አበባ
አመልካች:- ጎጎት ለጉራጌ አንድነት እና ፍትህ ፓርቲ (ጎጎት)
አድራሻ:- አ.አ አራዳ ክ/ከተማ ወረዳ 05 የቤት ቁ. አዲስ

ጉዳዩ:- በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 62 እና በአዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 24 እና 25 መሰረት የጉራጌ ህዝብ ለሦስት አመታት በፊት በክልል ለመደራጀት ያቀረበው አቤቱታ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት የቀረበ አቤቱታ ነው።

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌዴራሉ መንግስት አባላት ክልሎች የሚገኙት ብሄሮች፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የሚልኳቸው አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነው። ምክር ቤቱ በሀገሪቱን የህገች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነውን ህገ መንግስቱን የመተርጎም ፣ የብሄሮች ፣ ብሄረሰቦች እና ህዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ የመወሰን እና ሌሎች በርካታ ትልልቅ ሀገራዊ ኃላፊነቶች እና ሰልጣናች በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 62 እንዲሁም በአዋጅ ቁ. 1261/2013 መሰረት የተሰጠው ትልቅ ተቋም ነው።

የኢፌዲሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምር በርካታ ትልልቅ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ በማሰተላለፍ ለሀገሪቱ የህግ የበላይነት መዳበር እና በሀገ - መንግስታዊ ሰረአት የመተዳደር ልምድ እንዲዳበር የበኩሉን ድርሻ ሲወጣ ቆይቷል። ለአብነትም የ2012 ዓ.ም ምርጫ እንዲራዘም የሀገ መንግስት ትርጉም በመሰጠት ያስተላለፈው ውሳኔ፣ የትግራይ ክልል ምርጫ እንዲሰረዝ የወሰነው ውሳኔ፣ የሲዳማ ክልል እንዲቋቋም የወሰነው ውሳኔ በዋናነት የሚገለጹ ናቸው። ምክር ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀመር ከህገ መንግስት ትርጉም ተግባራቱ ጎን ለጎን የህዝቦች እኩልነትና በህዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ እንደነት እንዲዳብር እና በክልሎች መህከል የሚነሱት አለመግባባቶች መፍትሄ በመሰጠት በርካታ ሀገራዊ ሓይዲ ያላቸው ሰራዎች ሲሰራ ቆይቷል።

ከላይ የተዘረዘሩት የምክር ቤቱ ሀገራዊ አበርክቶዎች እንደተጠበቁ ሆነው ምክር ቤቱ ለቀረቡለት ጉዳዮች በህጉ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ፈጣን ምላሽ አለመሰጠት ደግሞ በተቋሙ ላይ የሚታይ ዋነኛ ችግር ነው። ከነዚህም መህከል ለዚህ አቤቱታው መነሻ የሆነው ላለፉት አራት አመታት ተገቢውን ምላሽ ያላገኘው እና የጉራጌ ህዝብ ለምክር ቤቱ ያቀረበውን በክልል የመደራጀት አቤቱታ ነው። በሀገሪቱ የህገች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነውን ህገ መንግስቱን የመተርጎም እና የመጠበቅ ሀላፊነት የተሰጠው ትልቅ ተቋም ያላከበረው ህገ መንግስት ሌላ ተቋምም ሆነ ግለሰብ ሊያከብረው ሰለማይችል የዚህ አቤቱታ መነሻ ይህንን መሰረት ያደረገ ነው።

የጉራጌ ብሄር በኢትዮጵያ ከሚገኙ ብሄር እና ብሄረሰቦች አንዱ መሆኑ የሚታወቅ ነው። የጉራጌ ህዝብ ከለውጡ በፊት በነበረው ዘመን በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት ውስጥ ከሌሎች 56 ብሄር እና ብሄረሰቦች ጋር በአንድ ክልል ተደራጅቶ መቆየቱን የሚታወቅ ነው።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ለአምስት አመታት በሽግግር ቻርተር ስትመራ ከልል 7 ተብሎ ይጠራ በነበረው ክልል ውስጥ ነበር። እሁን በሰራ ላይ ያለው ህገ መንግስት ሲጸድቅ የጉራጌ ህዝብ በደቡብ ብሄር ብሄረሰብች ክልል ውስጥ እንዲደራጅ መወሰኑን ምክንየት በማድረግ ጉራጌን ወክለው ሀዋሳ ላይ በተካሄደው ሰብሰባ የተገኙት የሀገር ሽማግሌዎች እና ታዋቂ ግለሰቦች በሰብሰባው የጉራጌ ህዝብ በዚህ ክልል መደራጀት እንደሌለበት ከፍተኛ ተቃውሞ ሲያሰሙ የወቅቱ ሰብሳቢዎች ሀሳባቸውን ሊቀበሏቸው ሰላልቻሉ ሰብሰባውን እረግጠው ለመውጣት ተገደዋል።

በዚህ መልኩ የጉራጌ ህዝብ ያለፍላጎቱ እና የሀገሪቱን የፌደራሊዝም መርህ በሚቃረን መንገድ ያለ ግዛት ክልሉ፣ ያለ ቋንቋ እንድነት፣ ያለ ማንነት እንድነት እና ያለ ሰነልቦና መቀራረብ በግድ ወደ እዚህ ክልል ተደራጅቶ እንዲኖር ተደርጓል። በዚህ ክልል ተደራጅቶ በነበረበት ወቅት ማንነቱ ተበርዞ፣ ቋንቋው ተዳከሞ፣ ባህሉ ተመናምኖ፣ በልማት ተጎድቶ እና በመልካም አስተዳደር እጦት ለችግር ተጋልጦ ኖሯል። ከዚህ በተጫማሪም የጉራጌ ህዝብ ለሀገር ካለው ውለታ እና ለፌደራሉ መንግስት ከሚከፍለው ግብር የማይመጣጠን በጀት እየተመደበለት በራሱ ሀገር እንደ ሌላ ሀገር ዜጋ በጭቆና ሲኖር ቆይቷል።

የጉራጌ ህዝብ ከላይ የተገለጹት ችግሮች እና ሌሎች በደሎች ተደራረበውበት መሸከም ሲያቅተው ህዳር 17/2011 ዓ.ም የዞኑ ምክር ቤት ባካሄድም አስቸኳይ ጉባኤ ህዝቡ መርጦ በወከላቸው በዞኑ ምክር ቤት የህዝብ እንደራሴዎቹ እማካኝነት እና በህገ መንግስቱ አንቀጽ 47/2 መሰረት በክልል ለመደራጀት በሙሉ ድምጽ ወሰኗል። የኢፌድሪ ህገ መንግስት እና የደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ህገ መንግስት ከሚደነግጉት መሰረት ውሳኔውን በተገቢው ጊዜ እና መስፈርቱን ባሟላ መንገድ በቁጥር 1697/ኢ.3 በቀን 21/03/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ ለክልሉ ምክር ቤት ቀርቦ ነበር። የክልሉ ምክር ቤትም በኢፌዲሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 47/3/ በፊደል ለ እና በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል ህገ መንግስት አንቀጽ 39/6 በፊደል ለ በተደነገገው መሰረት የዞኑ ምክር ቤት በክልል ለመደራጀት ያቀረበለትን ውሳኔ መርምሮ በአንድ እመት ጊዜ ውስጥ ህዝበ ውሳኔ ሊያደራጅ ይገደድ ነበር። ሆናም ግን የክልሉ ምክር ቤት ከላይ በተጠቀሱት የክልሉ እና የፌደራል ህገ መንግስቱ ድንጋጌዎች መሰረት በአንድ እመት ጊዜ ውስጥ መሰራት የነበረበት ሀለፊነቱን እና የስራ ግዴታውን አልተወጣም።

ይህንን መነሻ በማድረግ የኢፌዲሪ ህገ መንግስት በአንቀጽ 63/3/ እና በአዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 24 እና 25 በደገጉት መሰረት በክልሉ መንግስት የተፈጸመበትን በደል ህጋዊ መሰረቱን በጠበቀ መንገድ በቁጥር 4650/ኢ.3 በቀን 04/05/2012 ዓ.ም ለፌደሬሽን ምክር ቤት አሰፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን በማያያዝ እና የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጠው አቤቱታውን አቅርቦ ነበር። ሆናም ግን ህገ መንግስቱን የመተርጎም ትልቅ ህገራዊ ሀላፊነት የተጣለበት የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት ይህ አቤቱታ አሰከ ቀረበበት ጊዜ ድረስ ምንም አይነት ውሳኔም ሆነ ምላሽ አልሰጠም። ከሆኑ ተቃራኒ በሆነ መንገድ የምክር ቤቱ አፈ ጉባኤ በተለያዩ ሰብሰባዎች እና ጋዜጣዊ መግለጫዎች የጉራጌ ህዝብን ህገ መንግስታዊ መብት የሚደፈጥጥ ሀሳቦችን ሲያንጸባርቁ ቆይተዋል።

እሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ 56 ብሄር እና ብሄረሰቦችን ያቀፈው ነባሩ ደቡብ ክልል መፍረሱ ሚታወቅ ነው። የነባሩ ደቡብ ክልል ህገ መንገስትም ቢሆን ክልሉ ቀድሞ በነበረበት የህዝብ ቁጥር፣ የቆዳ ስፋት፣ የብሄሮች ብዛት እንዲሁም ቀድሞ በነበረበት የክልል ርዕሰ ከተማ ሰለማይገኝ ነባሩ ደቡብ ክልል እንደፈረሰ ሰለሚታሰብ የክልሉ ህገ መንግስትም ቢሆን ካልተሻሻለ በስተቀር ከአገልግሎት ውጪ ሆኗል።

እነዚህ ሁሉ እውነታዎችን ወደ ጎን በመተው የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ በቋሚ ኮሚቴው ያልተጣራ እና በምክር ቤቱ ውሳኔ ያለገኘ ሀሳብ በራሳቸው ፈቃድ በርካታ ጊዜ ሲያንጸባርቁ ቆይተዋል። አፈ ጉባኤው ከሌላው ዜጋ በላቀ መልኩ ሕገ መንግስቱን የማክበር እና የማሰከበር ሀላፊነት ተጥሎባቸው እያለ ያለ ሰልጣናቸው እና ህገ መንግስቱን በሚቃረን መንገድ የጉራጌ ዞን ምክር ቤትን ውሳኔ በሚቃረን መንገድ ነባሩ ደቡብ ክልል ባለበት ይቅጥላል በማለት ለሚዲያዎች የሰጡት ሀሳብ ሀላፊነት የጎደለው እና ኢ-ህገ መንግስታዊም ጭምር ነው።

ከዚህ በተጨማሪም ገዢው ፓርቲ ብልጽግና ህገ ወጥ በሆነ መንገድ የጉራጌ ዞን ምክር ቤት ቀድሞ የወሰነውን በክልል የመደራጀት ውሳኔ ሸር ማዕከላዊ ኢትዮጵያ በሚል ሲያሜ በሚቋቋመው አዲስ ክልል ለመካተት ውሳኔ እንዲያሳልፍለት እማራጭ እቅቦ ነበር። ቀድሞ ክልል ለመሆን በሙሉ ድምጽ በምክር ቤቱ የተወሰነው ውሳኔ ለመሻር በምክር ቤቱ የአሰራር መመሪያ መሰረት 2/3ኛ ድምጽ ያሰፈልግ የነበረ ቢሆንም ምክር ቤቱ ብልጽግና ፓርቲ ባቀረበውን እመራጭ ላይ ተወያይቶ 52 ለ 40 በሆነ ድምጽ ቀደም ሲል በክልል ለመደራጀት የተወሰነው ውሳኔ በመደገፍ እና የቀረበውን የክላስተር እማራጭ በፍጹም ጨዋ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ በደምጽ ውድቅ እደርጎ የወሰነበት ውሳኔ በደብደቤ እሰደገር ከነ ቃለጉባኤው በቁጥር 210/ክልል-4 በቀን 6/12/2014 ለኢፌድሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት አቅርቧል።

የፌደሬሽን ምክር ቤት ሰልጣን እና ተግባሩን ለመዘርዘር ተሻሽሎ በወጣው አዋጅ ቁጥር 1261/2013 አንቀጽ 25/4/ ሰር በተደነገገው መሰረት ክልል የመመሰረት ጥያቄው በደ/ብ/ብ/ህ/ክልል መንግስት በአግባቡ ባለማስተናገዱ ምክንያት የጉራጌ ዞን ምክር ቤት እቤቱታውን በጽሁፍ ከነ ዝርዝር ማስረጃዎቹ ከላይ በተጠቀሰው ወቅት ቀርቦለት ነበር። ለቀረበው እቤቱታ በሁለት እመት ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ግደታ እንዲለበት ተድንጎ እያለ ምክር ቤቱ የሚተረጉመው ህገ መንግስት እና ከላይ የተጠቀሰው አዋጅ በመጣስ እስከ ዛሬ ድረስ ምላሽም ሆነ ውሳኔ ባለመስጠቱ ይህ እቤቱታ እቤቱታው በፓርቲው ሊቀርብ ችሏል።

እነደ ኢትዮጵያ ባሉ በርካታ ብሄር እና ብሄረሰቦች በሚኖሩባቸው ሀገራት የፌደራሊዝም ሰርአት ተመራጭ የሆነ የመንግስት እውቃቀር ሰርአት ነው። በአለማችን በዲሞክራሲ ሰርአታቸው እና በኢኮኖሚያቸው የደበሩ እነደነ ካናዳ፣ ህንድ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ናይጀሪያ፣ ጀርመን እና ሌሎችም ሀገራት የሚከተሉት ያልተማከለ/ፌደራሊዝም/ ሰርአትን ነው። ናይጀሪያ ከኢትዮጵያ በፊዲ ሰፋት ያነሰች ሀገር ሆና እያለ ያሏት የክልሎች ብዛት 36 ደርሳዋል። ሌላዋ ትነሿ እውርጋዊት ፌደራሊስት ሀገር ሰዊዘርላንድ በ26 ክልሎች ተዋቅራለች። የጉራጌ ህዝብ ቁጥሩ መንግስታዊ በሆነ መንገድ በተደጋጋሚ ቢጭበረበርም በሀገራችን ብዙ ሚሊየን ቁጥር ካላቸው ብሄሮች እንዱ እንደሆነ ሁሉም የሚመስክረው ሀቅ ነው። የጉራጌ ህዝብ ቁጥር እና ሰፍር የሚገኝበት የመሬት ሰፋት በእለም ካሉት ሀገራት ከነሳነ ማሪና፣ ሌሰተንስታይን፣ ማልታ፣ ሞሪሽየስ፣ እንዶራ፣ ሲሸልስ፣ ኮሞርስ እና ሌሎችም ሀገራት የሚበልጥ ሰለሆነ የጉራጌ ህዝብ በክልል ለመደራጀት መጠየቁ ህገ መንግስታዊ ብቻ ሳሆን በቂ እሳማኝ ምክንያቶች ያለው እንደሆነ መገንዘብ ያሰፈልጋል። በሀገራችን በክልልነት ከዚህ ቀደም ከዚህ በተጨማሪም ከተደራጁት ክልሎች ከአብዛኞቹ በሰፋትም ሆነ በህዝብ ቁጥር እንደሚበልጥ ልብ ሊባል የሚገባው እውነታ ነው። የጉራጌ ህዝብ በክልል ለመደራጀት ያቀረበው ህጋዊ ጥያቄ በህገ መንግስቱ መሰረት ውሳኔ እና ምላሽ ካላገኘ ፌደራሊዝምን ከሚከተሉት ሀገራት በሙሉ በተግባር እና በእፈጻጸም የወደቀ ፌደራሊዝም /failed federalism/ በመከተል ምሳሌዎች ሊያደርገን የሚችልበት እድሉ ሰፊ ነው።

ጎጎት ለጉራጌ እንድነት እና ፍትህ ፓርቲ (ጎጎት ፓርቲ) በጉራጌ ህዝብ ላይ በመንግስት እየተፈጸሙ ባሉ ተደጋጋሚ በደሎች ምክንያት የብሄረሰቡን መብት ለማስከበር የተቋቋመ ፓርቲ ነው። ፓርቲው ከአሰራ ሦስት ሺ በላይ የድጋፍ ፊርማ በማሰባሰብ የምርጫ ቦርድ እዋጅ በሚያዘው መሰረት መሰፈርቱን አሟልቶ የተቋቋመ ፓርቲ ነው። ጎጎት ለጉራጌ እንድነት እና ፍትህ ፓርቲ ሀገራዊ ፓርቲ ቢሆንም የምሰረታ መሰረቱ የጉራጌ ህዝብ በመሆኑ በብሄረ ላይ የሚፈጸሙ የመብት ጥሰቶች የመለየት፣ የማሳወቅ፣ የመሞገት እና እንዲታረሙ የመታገል ግዴታ አለበት። በመሆኑም የጉራጌ ህዝብ በሀገራችን ያሉ ለሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች የተከበረላቸው በክልል የመተዳደር እና ክልላዊ መንግስት የመመስረት መብቱ ግልጽ ህገ መንግስታዊ ጥበት በሚታየበት መንገድ ውሳኔ ሳያገኝ ቆይቷል።

የፌደሬሽን ምክር ቤት በጉራጌ ህዝብ የክልል እደረጀጀት ጥያቄ ላይ የፈፀመው የመብት ጥሰት ለሚዲያ እና ሌሎች የፍትህ ተቋማት ከመቅረባቸው በፊት የጉዳዩ ባለቤት ለሆነው የኢፌዲሪ ፌደሬሽን ምክር ቤት ተቋም ህጋዊ በሆነ መንገድ እቤቱታ ማቅረቡ እሰፈላጊ መሆኑን ሰለሚያምን ይህ እቤቱታው ለምክር ቤቱ አቅርቧል። በመሆኑም የብሄር እና ብሄረሰቦች መብት የመጠበቅ እና የህገች ሁሉ የበላይ ህግ የሆነው ህገ መንግስቱን የመተርጎም ሰልጣን እና ሀላፊነት የተሰጠው የተከበረው የፌደሬሽን ምክር ቤት የጉራጌ ህዝብ ከሶስት እመት በፊት ያቀረበውን በክልል የመደራጀት ጥያቄ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እንዲሰጥበት በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከሰላምታ ጋር!

ጎጎት ለጉራጌ እንድነትና ፍትህ ፓርቲ
Gogot For Gurage Unity And Justice Party